# መደመር፣ ለስራ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ እንዲሁም ለመሰረታዊ ለውጥ !

በመጀመሪያ ደረጃ እዚህ ቆሜ በአገራችን ምድር ከአራት ወር ጀምሮ ስለሚካሄደው የፖለቲካ ለውጥና ተስፋ ሰጪ ሁኔታ አጭር መግለጫ እንድሰጥ ስለተጋበዝኩኝ የኢትዮ-በርሊንን አባላትና፣ በተለይም ለማህበሩ ሊቀመንበር ለአቶ ታደሰ ቶላ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ሁላችንም እንደምናውቀው ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ፣ እያንዳንዳችን የየራሳችንን ቡድን ወይም ድርጅት በመመስረትና በቀላሉ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ አጀንዳዎችን በማራገብ ዛሬ አገራችን ለደረሰችበት አስከፊ ሁኔታ በተለይም ዕድሜያቸን ከሃምሳ ዐመት በላይ የሆን የበኩላችንን አስተዋፅዖ እንዳበረከትን የማይታበል ሀቅ ነው። ህዝባችንና በተለይም ወጣቱ በማያውቁት ነገር ሰለባ በመሆን ፍዳቸውን እንዲያዩ ተደርገዋል። ወጣቱ አብዛኛው ህይወቱን ሲያጣ፣ የተቀረው ደግሞ ውጭ አገር ተሰዶ እንዲኖር ተገዷል።

አብዛኛውን ጊዜ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ውስጥ የማያስፈልጉ ግብግቦችና በቀላሉ መቋጠሪያ የማያገኙ የእርስ በእርስ ግጭቶች የሚፈጠሩት ካለመግባባትና ካለመደማመጥ የተነሳ ነው። አንደኛው የሌላውን ሃሳብ ሳይሰማና ሳይረዳ፣ ወይም ሰምቶ ወደ ሌላ ነገር በመተርጎም የማያስፈልግ ሁኔታ ይፈጠራል። በተለይም ግለሰቦች በቡድን በመሰባሰብ ራሳቸውን እንደልዩ ፍጡር አድርገው በሚቆጥሩበት አገርና፣ የሌላ ድርጅትን ወይም ግለሰብ አስተሳሰብ ለማዳመጥና ለመረዳት በማይፈልጉበት አገር ውስጥ እንደዚህ ዐይነቱ አለመግባባት ወደ ማያስፈልግ ሽኩቻ ያመራል። እንዳየነውና እንደኖርንበት ይህ ዐይነቱ የወንድማማቾችና የእህትማማቾች አለመግባባት የመጨረሻ መጨረሻ ሌላ አጀንዳ ላላቸው ቡድኖች አመቺ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። የታሪክ አጋጣሚን በመጠቀም አንድ ህዝብ ተስማምቶና ተፈቃቅሮ እንዳይኖር ያደርጋሉ።

ከዚህ ባሻገር አንዳንድ እናውቃለን የሚሉ ምሁራኖች የህብረተሰብአቸውን ታሪክ ለራሳቸው እንዲስማማ አድርገው በመተርጎም ለህብረተሰብአዊ ግጭት ምክንያት ይሆናሉ። በተለይም የተወሰነ የፖለቲካ አጀንዳን ይዘው የሚነሱ ኃይሎች የአንድን አገር ታሪክ ውጣ ውረድነት ሳይገነዘቡ በመቻኮል ወዳልሆነ ትግል ያመራሉ። እንደምናውቀው የዛሪይቱ ኢትዮጵያ ይህንን ዐይነት መልክ ለመያዝ የቻለችው እናቶቻችንና አባቶቻችን አገራችንን ሊወሩ የመጡትን የውጭ ጠላቶችን መክተው በመመለሳቸው ነው። በተለይም አፄ ቴዎድሮስና አፄ ምንሊክ ኢትዮጵያን ዘመናዊና ጠንካራ አገር አድርገው ለመገንባት ያላደረጉት ጥረትና ትግል የለም። በጊዜው በነበረው ደካማ የህብረተሰብ አወቃቀርና ንቃተ-ህሊና ማነስ ምክንያት የተነሳ ምኞታቸው ሙሉ በሙሉ ባይሳካም ለአንድነት ያደረጉት ትግል ለተከታታዩ ትውልድ ውስጣዊ ኃይል ሰጥቶታል ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብሰብ ሲልና ሲተባበር ቋንቋውን በተሻለ መልክ ማዳበር ችሏል። በተጨማሪም በልዩ ልዩ መልክ የሚገለጹ ባህሎች የመሰባሰባችንና የውህደታችን ውጤቶች ናቸው። በማንኛውም የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ እንደተረጋገጠው በአንድ አገር የሚኖር ህዝብ ሰብሰብ ሲል ብቻ ነው ብሄራዊ ስሜቱ ሊዳብር የሚችለው። ማንነቱንም ሊያውቅና ራሱንም የሚችለው በክልል ደረጃ ሳይሆን ራሱን የጠቅላላው ህብረተሰብ አካል አድርጎ የቆጠረ እንደሆን ብቻ ነው። ስለሆነም የዚህ መተባበር ውጤት እንደ አማራኛ ቋንቋን የመሰለ ሁሉንም የሰዋስው ህግ የሚያሟላ መዳበር መቻሉ የረጅም ጊዜ ትግል ውጤት ነው። በተጨማሪም የተለያዩ የምግብ ዐይነቶች መፈልሰፍና መዳበር፣ እንደ ጠላና ጠጅ እንዲሁም ካቲካላ የመሳሰሉት የባህል መጠጦች መፈጠር፣ የልብስ ስራና እነዚህና ሌሎች ባህሎች በሙሉ ብሄራዊ ባህርይ መውሰድ የአንድ ብሄረሰብ ውጤቶች ሳይሆኑ የሁሉም ብሄረሰቦች ተሳትፎ ውጤቶች ናቸው። በተለይም ደግሞ ከ1920ዎቹ ዓመታት ጀምሮ ዕምርታን ያገኘው የአገራችን ሙዚቃ የትብብራችንና የውህደታችን ውጤት ነው። የተለያዩ በመሳሪያ የታጀቡ የአገር ባህልና ዘመናዊ ሙዚቃዎች የማንነታችን መግለጫዎች በመሆን የበለጠ እንድንቀራረብና እንድንዋሃድ አድርገውናል። የኢትዮጵያ አርበኞች ለሁለተኛ ጊዜ በጣሊያን የተቃጣባቸውን ጦርነት በመመከት ድል ከተቀዳጁ በኋላ የተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ብሄራዊ ባህርይ ላለው የሙዚቃ ቅኝትና ዜማ መዳበር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ማለት ይቻላል። ስለሆነም 1950ኛው ዓ.ም የኢትዮጵያ የሙዚቃ ሬናሳንስ ወይም የተለያዩ የሙዚቃ ስልቶች የዳበሩበትና የተስፋፉበት ዘመን ነበር ማለት ይቻላል። ሌሎች እንደ ኳስ ጫወታና የአትሌቲክስ ውድደሮች መዳበርና መስፋፋት በሙሉ የሚያረጋግጡት በእርግጥም አገራችን ብሄራዊ ባህርይ የያዘችበት ዘመንና ማንኛውም ዜጋ ራሱን ለመግለጽ ሰፋ ያለ መድረክ ያገኘበት ጊዜ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።

ይህንን ሁሉ የማነሳው አብዛኛውን ጊዜ የታሪክን ሂደትና የህዝቦችን ትግልና ሲተባበሩ የሚፈጥሩትን ካለመገንዘብ የተነሳ የማይገባ ግጭት ተፈጥሮ ታሪክን ወደ ማፈራረስ ሊያመራ እንደሚችል ለማስገንዘብ ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ ብሄረሰብ ብቻ በሌሎች ብሄረሰቦች ላይ የራሱን ፍላጎት የጫነበት ዘመን አልነበረም። ይሁንና ግን አገዛዙ ካለብዙ ጥናት ተግባራዊ ያደረገው የኢኮኖሚ ፖሊሲና የሰራው የፖለቲካ ስህተት በጠቅላላው አገሪቱ ውስጥ ሰፋ ያለ

ህዝቡን ሊጠቅምና የኑሮ ደረጃውን ሊያሻሽል የሚችል ሀብት ሊዳብር አልቻለም። በዚህም ምክንያት የተነሳ በጠቅላላው አገራችን ውስጥ የተዘበራረቀና የአልተስተካከለ ዕድገት ይታይ ነበር። ይህ ዐይነቱ ሁኔታ ለአንዳንድ ኃይሎች የአገራችንን ታሪክ ራሳቸው በመሰላቸው መንገድ እንዲተረጉሙ መንገዱን አመቻቸላቸው። የብሄረሰብ እንቅስቃሴዎች የሚባሉ እዚህና እዚያ ብቅ በማለት የህብረተሰባችንን መንፈስ ለመረበሽ ቻሉ። በእናቶቻችንና በአባቶቻችን የተገነባው የብዙ መቶ ዐመታት ባህልና እሴት ቀስ በቀስ መበጣጠስ ጀመረ። ሁላችንም የጎሪጥ ለመተያየት በቃን።

ከዚህ ስንነሳ በተለይም ባለፉት 27 ዓመታት አገራችንና ህዝባችን ፍዳቸውን እንዲያዩ ተደረገዋል። ከአንድ ብሄረሰብ የተውጣጡ ጥቂት ግለሰቦች ብሄረሰባችንን እንወክላለን በማለት በታሪካችንና በህዝባችን ላይ ብቻ ሳይሆን በራሳቸውም ታሪክና ባህል ላይ ዘምተዋል። ዛሬ የምንጠቅምበት የአማርኛ ፊደልና የምንቃኘው ሙዚቃ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ዛሬ ትግሬ ተብሎ በሚጠራው ቦታ በጊዜው በነበሩ አገዛዞችና ህዝቦች የተፈጠሩ ናቸው። እነዚህ ናቸው ለዛሪይቱ ኢትዮጵያ መሰረት የጣሉትና በልዩ ልዩ መልክና ቃና የሚገለጹ ሙዚቃዎችና የአነጋገር ስልቶች ሊዳብሩ የቻሉት። ይህንን ካለመረዳት የተነሳ የህወሃት አገዛዝ፣ በአብዛኛዎቻችን ዘንድ ወያኔ በመባል የሚታወቀው ኃይል በራሱ ባህልና ታሪክ ላይ በመዝመት ነው ህዝባችን እርስ በእርሱ እንዳይተማመንና፣ እንዲያም ሲል ወደ እርስ በእርስ ጦርነት እንዲያመራ ያደረገው። ይሁንና ግን በህዝባችን ቻይነትና አርቆ-አስተዋይነት የተነሳ የታለመው ዕቡይ ዓላማ የመጨረሻ መጨረሻ ግቡን ሊመታ አልቻለም። በተለይም በአለፉት 27 ዓመታት ይህንን ዐይነቱን አካሄድ የሚቃወምና በታሪኩ የሚኮራ አዲስ ትውልድ በመፈጠሩ የዛሬውና ተሰፋ ሰጭ ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። „እግዚአብሄር ሳይደግስ አይጣላም" እንደሚባለው አነጋገር የመጨረሻ መጨረሻ ኢትዮጵያችንን አልከዳትም። ስለሆነም የኦሮሞው፣ የአማራው፣ የጉራጌውና የሌሎች ብሄረሰቦች ወጣቶች ባካሄዱት ቆራጥና አርቆ-አስተዋይነትን ያካተተ ትግል አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ገብተናል ማለት ይቻላል።

ከስድስት ወራት በፊት አንዳችንም ብንሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ በአገራችን ምድር እንደዚህ ዐይነት አስገራሚና ደስ የሚል ሁኔታ ይፈጠራል ብለን አላሰብንም። በተለይም የግንቦት 1997 ዓ.ም እጅ ውስጥ የገባ የምርጫ ውጤትና የአገዛዙ መደናበር በመከሸፉ አብዛኛዎቻችን ተስፋ እስከመቁረጥ ደርሰን ነበር። ከዚያም በኋላ በተለይም የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ በኦሮሚያና በጎደንር የተነሳውን እንቅስቃሴና ግጭት አስመልክቶ ለጊዜው ተስፋችን ጭላንጭል ቢያገኝም ከሌላ ቦታ ትብብር ባለመገኘቱ ያ እንቅስቃሴ ለጊዜውም ቢሆን በመገታቱ እንደገና ተስፋ እንደቆረጥን የማይካድ ነበር። ስለሆነም የህዋሃት አገዛዝ ለረጅም ጊዜ እንደሚቆይና በመከፋፈልና ህዝባችንን እርስ በእርሱ በማጋጨት ተግባሩ እንደሚገፋበት ድምዳሜ ላይ ደርሰን ነበር። ይሁንና ግን ራሱ አገዛዙ የፈጠረው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች፣ እንዲሁም የጭቆናው መብዛትና በተደጋጋሚ ይሰራ የነበረው የፖለቲካ ስህተቶች በኢህአዴግ ውስጥ የውስጥ ለውስጥ ሽኩቻውን እንዳባባሰው የማይካድ ሀቅ ነው። ስለሆነም በዚህ ዐይነት ሁኔታ መቀጠል እንደማይቻል የተረዱና አንዳንድ የተገለጸላቸው ኃይሎች ሁኔታው ገፍቶ እንዲሄድ በማድረግ የመጨረሻ መጨረሻ የጠቅላይ ሚኒስተር ኃይለማርያምን ከስልጣን ማስወገድ አስከተለ። ሌላ አማራጭ ማቅረብ የማይችለው የህወሃት አገዛዝ  የግዴታ የዶ/ር አቢይን ጠቅላይ ሚኒስተር ሆኖ  በብዙ ድምጽ ብልጫ መመረጥን የግዴታ ተቀበለ።

ዶ/ር አቢይ ስልጣንን ሲረከቡ ያደረጉትን የመክፈቻ ንግግር ሁላችንም በአንክሮት አድምጠነዋል። ያነሱትና ያተኮሩት በልዩነቶቻችን ላይ ሳይሆን በሚያገናኙን ነገሮች ላይ ነው። ሁላችንም በጋራ የምንሰራቸው ብዙ የቤት ስራዎች ስላሉን ምንም የሚያጣላንና የሚያጋጨን ነገር የለም የሚል ነው። ኢትዮጵያ የምትባለው አገር የሁላችንም መሆኗን አጠንክረው በማንሳት፣ ልንነሳም ልንወድቅም የምንችለው አንድ ላይ በመሆን ብቻ ነው የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል። በሌላ ወገን ግን የሁላችንም ፍርሃት የነበረው ዶ/ር አቢይ እንዴት አድርገው  ህወሃት የገነባውን የፀጥታ ኃይልና፣ አግአዚን የመሰለ ፋሺሽታዊ ጦርና የወታደሩን ተቋም ሊያሻሽሉ ይችላሉ ? የመንግስት ግልበጣስ ሊፈጠር አይችልም ወይ? የሚል ነበር ስጋታችን። በሰውየው ጥበብ የተነሳና ራሱ ህውሃት ውስጥ የተፈጠረውን መደናገጥ በመጠቀም ዶ/ር አቢይ በአጭር ጊዜ ውስጥ የህወሃትን የበላይነት ለማዳከም ችለዋል። ሁሉኑም ባይሆን እንኳ ለጥገና ለውጥ እንቅፋት የሚሆኑ አንዳንዶችን የመከላከያና የፀጥታ ሹማምንቶችን ከስልጣን አስወግደዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁላችንም ያልጠበቅነውንና ማንም ኃይል ሊያደርግ የማይችለውን ሳይፈሩ ሳይቸሩ አስፈላጊ ስራዎችን ሰርተዋል። አሁን በቅርቡ ከኤርትራ አገዛዝ ጋር ያደረጉት የዕርቅ ስምምነትና ራሳቸውም አስመራ ድረስ ሄደው ከፕሬዚደንት ኢሳያስና ከተቀሩት መሪዎች ጋር መገናኘት ይህ ሁሉ የሚያረጋግጠው ኢትዮጵያችን አዲስ ምዕራፍ ውስጥ እንደገባች ነው። በአንፃሩም ፕሬዚደንት ኢሳያስ አዲስ አበባ ድረስ መምጣታቸውና ልዩ ዐይነት አቀባበል እንዲደረግላቸው መደረጉ የሚያረጋግጠው የዶ/ር አቢይን ብልህ መሪነት ብቻ ሳይሆን ሁለቱም፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዞቦች ከእንግዲህ ወዲህ የሚሹቱና የሚመኙት ሰላምንና ፍቅርን፣  እንዲሁም በጋራ ተነስቶ አገርን መገንባት ብቻ እንደሆነ ነው። በሌላ ወገን ግን ይህ ዐይነቱ ለውጥ ያላስደሰታቸው የህዋሃት መሪዎችና የስለላ ሰዎቻቸው በአገሪቱ ውስጥ የእርስ በእርስ ጦርነት እንዲነሳ

ያላደረጉትና የማያደርጉት ሙከራ ይህ ነው አይባልም። በመስቀል አደባባይ ላይ በተጠራው የመደመር ሰልፍ ላይ በተገኙት ጠቅላይ ሚኒስተር አቢይና ሌሎች ባለስልጣኖች ላይ የተሰነዘረው ጥቃት የሚያረጋግጠው ዶ/ር አቢይን በማስወገድና ስልጣንን እንደገና በመጨበጥ የጭቆናውንና  የብዝበዛውን ዘመን ለማራዘም ነበር። እንደ ኢጋጣሚ ሆኖ ሁኔታውን የጠረጠሩ ሰዎች ሊፈነዳ የተዘጋጀውን ፈንጂ ነገር ህይወታቸውን በመሰዋት ባያከሽፉት ኖሮ የዶ/ር አቢይና የተቀሩትም ባለስልጣናት ህይወት ሊተርፍ አይችልም ነበር። ይህን ኢጋጣሚ በመጠቀምና የነገሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ ዶ/ር አቢይ የጸጥታ ሹሙንና የአዲስ አበባ ፖሊሲ ኮሚሺነሩንና ሌሎችንም ከስልጣናቸው አባረዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተወሰዱትና የሚወሰዱት እርምጃዎች የተጀመረው ለውጥ በቀላሉ ሊቀለበስ እንደማይችል አድርገውታል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ደስ የሚል ሁኔታ ስንነሳ የኛ ሚና ምን መሆን አለበት ? ሚናችን መደመር ብቻ ነው። ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው። በጋራ ተነስተንና እጅ ለእጅ ተያይዘን አገርን መገንባትና በኢትዮጵያ ምድር ዘለዓለማዊ ሰላምን ማስፈን ነው። እንደሚታወቀው ዛሬ በለጸጉ የሚባሉ አገሮች በሙሉ እዚህ ዐይነቱ የዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት በመናቆር ወይም አንደኛው ለሌላው እንቅፋት በመሆን ሳይሆን በጋራ በመነሳት ነው። ታሪክ እንደሚያረጋግጠው አንድ ህዝብና ምሁሮች ሲተባበሩና ለጋራ ዓላማ ሲቆሙ ተዓምር መስራት እንደሚችሉ ነው። ያልተባበረና ራሱን የማይጠብቅ ህዝብ ሁልጊዜ በቀላሉ በውጭ ኃይሎች እንደሚታለልና የመጨረሻ መጨረሻም እንደሚጠቃ የአገራችንና የሌሎች አገሮች ታሪክ ያስተምረናል። በሌላ ወገን ግን መደመር ማለት ዝም ብሎ  አብሮ መንጋጋት አይደለም። በተለይም የተጀመረው የለውጥ ሂደት መሬት እንዲረግጥና በህዝባችንም ላይ መሰረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ከተፈለገ የግዴታ ጥራትን የሚጠይቅ ነው። የዛሬውን የመደመር ሁኔታ በመጠቀም ሁሉም ተንጋግቶ በመግባት ብዙ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል። ስለሆነም  በሃሳብ ዙሪያ ግልጽና የማያወላዳ ክርክር መደረግ አለበት። በተለይም የኢኮኖሚ ፖሊሲን በሚመለከት የተለያየ አተረጓጎም ስላለ በዚህ ዙሪያ የማያቋርጥና ጥራት ያለው ስራ መሰራት አለበት። ለውጥ ሲባል ምን ማለት እንደሆነና ማንስ የለውጥ ኃይል ሊሆን እንደሚችል ሁሉም ያለውን አስተሳሰብ በገሃድ ማሳየት ያለበት ይመስለኛል። ምኞታችንና ዋናው ዓላማችን ጠንካራ ኢኮኖሚ በመገንባት የህዝባችንን ህይወት ለማሻሻል ስለሆነ በተለይም ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው ሰዎችና ቡድኖች ሳይፈሩ ሳይቸሩ አስተያየታቸውን መሰንዘር አለባቸው። ተደማጭነት ለማግኘት በየጊዜው በጠራ መልክ አስተያየታቸውን ማቅረብ አለባቸው።

እንደሚታወቀው በአገራችን ከጠቅላላው ህዝብ ውስጥ አብዛኛው ወጣት ነው። ወጣት ትውልድ ደግሞ የአረጀውን ትውልድ ተኪ እንደመሆኑ መጠን ከፍተኛ እንክብካቤ ያስፈልገዋል። አገሩን ለማበልጸግና ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላልፍ ዘንድ በሁሉም አቅጣጫ መሰልጠን አለበት። ስለሆነም የዚህ አዲስ ትውልድ ምኞትና ህልም ሰላም፣ ፍቅርና ጤናማ ዕድገት ናቸው። ይህ ትውልድ ውስጣዊ-ኃይሉ ከፍ ያለ ስለሆነ የሚፈልገው ጭቅጭቅንና ተንኮልን ሳይሆን ሰርቶ የሚያሳየውን ነው። የሚመኘው አዲስና የሰለጠነች ኢትዮጵያን ነው። ስለሆነም ብዙ ጭቅጭቅ ውስጥ ሳንገባና ውሎ ሳያድር በስራ ላይ መሰማራት አለብን። ለዚህ ለደግሞ ለአገር ግንባታ የሚሆኑ የእርሻ ምርቶችና ልዩ ልዩ የሆኑ የጥሬ ሀብቶች አሉን።

ሁላችንም እንደምናውቀው በአገራችን ምድር የተለያዩ የሰብል ዐይነቶች ይበቅላሉ። ስንዴና ገብስ፣ ማሽላና ዘንጋዳ፣ ጤፍና ዳጉሳ፣ እንዲሁም አጃና ሌሎች የጥራ ጥሬ እህሎችና ለዘይት የሚያገለግሉ እንደኑግ፣ ተልባ፣ ሰሊጥና ሱፍ የመሳሰሉት በብዛት በአገራችን ምድር ይበቅላሉ። በተጨማሪም እንደ ድንች፣ ወጭኖና ጎደሬ እንዲሁም እንሰት የመሳሰሉትና አያሌ የፍራፍሬ ዐይነቶች፣ ፓፓዬ፣ ማንጎ፣ትርንጎ፣ሎሚ፣ ብርቱካንና ሙዝ በብዛት ይበቅላሉ። ከዚህም ባሻገር እንደ እንጆሪ፣ ዶቅማና የሾላ ፍሬ የመሳሰሉት በብዛት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወፍ ዘራሽ በሆነ መልክ በቅለው ይገኛሉ። እንዲሁም የተለያዩ የቀንድ ከብቶች አሉን። እንደሚታወቀው 85 % የሚሆነው ህዝባችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኑሮው ከእርሻ ምርትና ከከብት እርባታ ጋር የተያያዘ ነው። ስለሆነም ገበሬው በአንድ በኩል ምርታማነቱን እንዲያሳድግ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የኑሮውን ሁኔታ እንዲያሻሽል ወለዱ ዝቅተኛ የሆነ ብድር፣ ምክርና የምርት መሳሪያዎች እንዲሰጠውና እንዲቀርብለት ያስፈልጋል። ገበሬው አብዛኛውን ህዝብ መጋቢ እንደመሆኑ መጠን በእርሻው ላይ የሚደረገው እርብርቦሽ የአገራችንን የወደፊት ዕድል ይወስናል። ከዚህ ባሻገር ከተማዎችን ለመገንባትና ቤቶችን ለመስራት የሚያገለግሉ የተፈጥሮ ሀብት አሉን። ለጡብ የሚሆን የብረትነት ይዘቱ ከፍ ያለ አፈር፣ የተለያየ የዲንጋይ ዐይነት፣ እነዚህን ሊያጣብቅ የሚችል ኖራ፣ ጀሶና ደለል በብዛት በአገራችን ምድር ይገኛሉ። እነዚህን ቆፍረን በማውጣት በስርዓት የምንጠቀም ከሆነ በሃያና በሰላሳ ዐመታት የአገራችንን ስዕል መለወጥ እንችላለን። በተጨማሪም የአገራችን የምድር አቀማመጥና የአየር ሁኔታ ለመሰረታዊ ለውጥ የሚያመች ነው። ለዚህ ሁሉ ግን ስርዓት ያለው ዕቅድና ቆርጦ መነሳት እጅግ አስፈላጊ የዕድገት መሰረተ-ሃሳቦች ናቸው። ይሁንና ግን በአገራችን ውስጥ ፈጣን ዕድገት ለማምጣት ከተፈለገ የግዴታ ሁሉም እንደአቅሙ የገንዘብ ዕርዳታ ማድረግ አለበት። ይህንን አስመልክቶ የዶ/ር አቢይ አገዛዝ

በተለይም ውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ትረስት ፈንድ በሚል ስም የባንክ ቁጥር ከፍቷል። ስለዚህም ሁላችንም የዶ/ር አቢይን ጥሪ በመቀበል አስፈላጊውን መዋጮ እንደምናደርግ ተስፋ አለኝ።

ለማንኛውም ካለፉት አራት ወራት ጀምሮ በአገራችን ምድር የተከሰተው አዲስ ሁኔታ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ነው ማለት ይቻላል። የመጀመሪያ የሚያሰኘው የዶ/ር አቢይ አህመድ ከዚያ ረመጥ ውስጥ ብቅ ብሎ መውጣት ነው። በተጨማሪም አገራችን ባለፉት ስድሳ ዐመታት እንደዚህ ዐይነት ብሩህ ሰው፣ ዲሞክራትና ግልጽ በሆነ መልክ የሚናገር መሪ አግኝታ አታውቅም። ሶስቱም ያለፉት አገዛዞች ህዝባዊ ባህርይ የሌላቸውና ከህዝብ ጋር ቀርበው የሚነጋገሩ አልነበሩም። ስለሆነም ይህ ዐይነቱ ዕድል እንዲሳካ ኃይላችንን ማስተባበርና ለስራ ታጥቀን መነሳት አለብን። በአሁኑ ወቅት ከትብብርና ከድምር ውጭ የጊዜያዊ መንግስት መቋቋም አለበት ወይም ምርጫ መካሄድ አለበት እያሉ የሚወተውትበት ጊዜ አይደለም። በአገራችን ምድር የተቆላለፉና የተደራረቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የጎሳ ችግሮች አሉ። እነዚህን ሁሉ ችግሮች ቀስ በቀስ ለመቅረፈና ለህዝባችንም አስተማማኝ የዕድገት መሰረት ለመጣል የምንችለው በቡድን በቡድን በመደራጀትና ለስልጣን በመታገል ሳይሆን በጋራ በመተጋል ብቻ ነው። ህዝባችን መከፋፈልን አይፈልግም። ህዝባችን የሚፈልገው እየሰራ የሚያሳየውን ነው። ህዝባችን የሚመኘውና የሚፈልገው የኑሮው ሁኔታ እንዲሻሻልለት ነው። ስለሆነም ንጹህ ውሃን መጠጣት ይፈልጋል። ጥሩ ቤት ውስጥ መኖርን ይመኛል። መንደሮቹና ከተማዎቹ በጥሩ መልክ እንዲገነቡለት ይፈልጋል። በአካባቢው ክሊኒኮችንና ትምህርት ቤቶችን ይሻል። በአጭሩ ከዛሬው አሳፋሪ ሁኔታ ተላቆ አዲስ ህይወትን ማየትና መኖርን ይፈልጋል። እነዚህን የህዝባችንን ፍላጎቶችና የረጅም ጊዜ ምኞቶች መፍታት የሚቻለው በተናጠል ሳይሆን በጋራ ብቻ ነው። ሌላ የተደበቀ ዓላማ እስከሌለን ድረስ እነዚህን ነገሮች በአስርና በሃያ ዐመታት ጊዜ ውስጥ ዕውን ልናደርጋቸው እንችላለን። ከጀርመን፣ ከደቡብ ኮሪያ፣ ከጃፓንና ከቻይና መማር እንችላለን። በሌላ አነጋገር ***„ድር ቢያብር አንበሳ ያስር"*** እንደሚባለው አነጋገር በመነጣጠል ሳይሆን አዲሲቷን ኢትዮጵያ የምንገነባው በመተባበር፣ ሃሳብ ለሃሳብ በመለዋወጥ፣ በመደማመጥና በመከባበር፣ እንዲሁም በመከራከር ብቻ ነው። ለዚህ ሁሉ ሀቀኝነት፣ ስነ-ምግባር፣ ግብረ-ገብነት፣ ከተንኮል የፀዳ መንፈስ፣ መደጋገፍና መተባበር እጅግ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ሃሳቦች ናቸው። እነዚህን እንደ ዋና መሰረተ-ሃሳቦችና ባህሎቻችን አድርገን በመቁጠር ከደማችን ጋር በማዋሃድ ልጆቻችንም ማስተማር አለብን። ሁላችንም በቆንጆ አስተሳሰብ በመታነፅ ቆንጆ ኢትዮጵያን ለመገንባት ቆርጠን ካልተነሳን በስተቀር በቀላሉ ሊረሳ የማይችል ከፍተኛ የታሪክ ወንጀል ሰርተን እንዳለፍን ይቆጠራል። ስለአዳመጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ !!

**ፈቃዱ በቀለ**

28.07.2018